# <u>የት ደርሰናል? --ክፍል ሁለት</u>

ከአረቷ ተካ

ትላንት ዛሬን አይሆን ብሎ ሕዝቡ ሲያምፅ
አለቀ ደቀቀ ስርዓት ይላል ድርምስ።

የተባለው የዘወትር ሀቅ ነውና ዛሬ ለውጥን ያረገዘው ሁኔታ በእርግጥም እየጠበቀ ያለው የተደራጁ ክፍሎችን አለን በአመፅ የሚል መልዕክትና ዝግጅነት ነው። የተጨቆነ ሕዝብ ምንኛ ቢመረውና ቢከፋው ካልተደራጀ በተደራጀው ጠላቱ ላይ ድልን ሊቀዳጅ አይችልም። የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ የጥቂቶች ነው። ይደግፈኛል ብሎ የሚጠራው የትግራይ ሕዝብ ራሱ በአብላጫው አይፈልገውም። በሌላ በኩል ደግሞ የማይካደው ሀቅ ይህ አገዛዝ የእኛ ነው ብለው በአገዛዙ ላይ የሚመጣ ጥቃት ሁሉ በትግራይ ተወላጆች እንደመጣ አድርገው የሚወስዱ ወደዱም ጠሉም የመለስን አገዛዝ የሚደግፉ የትግራይ ተወላጆች መኖራቸው የሚታወቅ ነው። አገዛዙ በመሰረቱ የሕዝብ ሰፊ ድጋፍ የሌለው የተጠላ ቡድን በመሆኑ ክንዱ ወይም አቅሙ ደካማ ነው። ይህን ችግሩን ስለሚያውቅ ግን ሕዝብ እንዳይደራጅ ወይም የተደራጁት ተባብረው እንዳይጠናከሩ የአቅሙን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም።

በዚህም መሰረት አገዛዙ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ነቃ ብሎና ተግቶ እየሰራ ያለ መሆኑ ይታያል። በቅድሚያ ህዝብን የሚያፍንበትን ተቋሞች ሁሉ ለማጠናከር እየጣረ ነው። የማይተማመንባቸውን ጄኔራሎችና መኮንኖች ከጦሩ አባሯል። ታማኝ ወጣቶችን ከትውልድ ቦታው በስፋት መልምሏል። በገንዘብና ሹመት ደለላውን አጧጡፏል። ከባዕዳን ገንዘብና ወታደራዊም እርዳታ ለማግኘት እየተሯሯጠና እያገኘም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎች ለሆዳቸው ይገዛሉ የሚል የንቀት አስተሳሰብ ሰላለው በተለይም በባዕድ ሀገር ያለውን ማህበር መስርታችሁ መሬት ተመሩ፣ ነግዱ ወዘተ በሚል ደልሎ ለመያዝና ከተቃዋሚ ጎራ ለማዉጣት እየተረባረበ ነው። ሀገር ቤት ሄደው መሬት ተመርተውና ቤት ገዝተው/መስራት ጀምረው የሚመጡትን በአብዛኛው ሰናይ ከወደ ታቀውሞው ደከም እያሉና በንብረታቸው የተነሳ በወያኔ ቆንጠጥ ሲደረጉ ደግሞ ወይ ዝም፣ ወይ እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው ምን ማድረግ ይሻላል እያሉ ሸርተት ሲሉ ወይም ከባሰም የተቃዋሚውን ጎራ የሚበጠብጡ ወደመሆኑ ሲያመሩ አልታዘብንም ማለት አይቻልም። የምስጢር ስሪት ቅጥረኞቹን በመጠቀምም ተቃዋሚ ድርጅቶችን ሰርጎ በመግባት ለማበጣበጥና ይበልጥ ለመከፋፈልም እየጣረ ነው። ይህ ሁሉ ጭራሽ ውጤት አልባ ነው ማለት አይቻልም። የተወሰነ ደረጃ ማጋነን ቢታከልበትም ከ30 ያላነሱ ግለሰቦች ከሻዕቢያና ከቦንብ ፍንዳታዎች ጋር በተየያዘ በቁጥጥር ስር መግባታቸው የሚካድ አይደለም። ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች እንዳጋለጡት ሁሉ ከ60 በላይ ዜጎች በፀረ ሽብር ፖሊስ መያዛቸውና ብዙዎቹም መደብደባቸው ወይም ቶርች መደረጋቸው ታውቋል። በሚመለከተው የፖሊስ ክፍል ገለፃ መሰረት ተብሎ ከተዘገበው ዝርዝር ስንነሳ ደግሞ ከተያዙት ውስጥ አብዛኞቹ ወጣቶቹ ሲሆኑ 40 ያህሉ የቅንጅት አባላት፣ 8 የኦነግ አባል የተባሉ፣ 4 የኢሕአፓ የሽብር ቡድን አባሎች የተባሉ፣ 3 የቀድሞ ወታደሮች፣ 1 ኤርትራዊና ሌሎችም እንዳሉበት ታውቋል። ወያኔ ሰፊና የተቀነባበረ ሴራ ሊካሄድብኝ ነበር ወይም አሁንም እየተካሄደብኝ ነው ቢልም፣ በዚህም በዚያም ሙከራዎችና ጥረቶች የሚታዩ ቢሆንም ተቃዋሚዎች በተቀነባበረና በተቀናጀ መልክ እየሰሩ ነው የሚያሰኝ መረጃ የለም። በውስጡ ውስጥ ዓለም ሳይወዱ ቢገናኙም ሲያብሩ ገና አልታየም። የተሞከሩት ፍንዳታዎች ሲታዩም ወያኔን ሳይሆን ንፁሁን ዜጋ የጎዱ መሆናቸው ደግሞ ታይቷል።

በሽታችንን ከራሳችን ከደበቅን ለህክምና እንደማያመች ግልፅ ነው።ያለውን የአገዛዙን ድክመት ተጠቅመን የሚወገድበትን ትግል ለማድረግ ያልቻልነው አሰባበሳቢባ አዳርጅ የሆነ ድርጅት ወይም ድርጅቶች በማጣታችን ም። በመሳባሰብ ፈንታ መከፋፈል ሰፍኖ ጠንካራ ነን ይሉ የነበሩ ድርጅቶች ሲከፋፈሉ አይተናል። ቅንጅት ተከፋፍሎ ይናከሳል። ህብረቱ ፈዟል።ትጥቅ ትግል ጀመርን ያሉት በለስ እንዳልቀናቸው ደግሞ የባዕድ ጋዜጦችም ሳይቀሩ እየነገሩን ነው። በዚህም በዚያም ደግሞ የትጥቅ ትግሉ አማራጭ በርከት እያለ መምጣቱ የሚታይ ነው። የኦነግ አመራሮች የመረውን የዳውድ ኢበሳ መስመር ተቃውመው በኢትዮጵያዊነት ክልል የኦሮሞን ህዝብ መብት እናስከበር

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እያሉ ነው ተብሎ በጋዜጣ የተዘገበውም ተስፋ ሰጪ ሆኗል። በአንፃሩ ግን ዛሬም ያበቃለትን መደናገር አዝለው በፈረንጅ የሚተማማኑና በመጪው ምርጫ ተሳትፈው ወያኔን በአሜሪካ ድጋፍ ሊያሸንፉ የሚያልሙ መኖራቸው መጠቀስ ያለበት ነው። በደም በመከራ በስቃይ የተገኘን ትምህርት እስከመቼስ እምቢ አልሰማም ማለት ይቻላል? ስለዚህም ይህን ማድረግ ይገባል ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ መልስ እንስጥ ካልን በመጀመሪያ የራሳችንን ድክመት በሚገባ ማወቅና ማመን ይኖርብናል። ሕዝብ ለትግል ዝግጅ ሆኖና መስዋዕትነትንም ሊከፍል ቆርጦ ተነስቶ እያለ ትግል ሊዳከም አይችልም። ድርጅቶች የታሰረ አንበሳ በብላሽ አገሳ እንዳይገሉ መንቃት መሰባሰብ አለባቸው ማለት ነው።

ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ ማለት የሚወዱት አንዳንዶቹ ዛሬ ከወያኔ አብረው ቢገኙም የህብረትን ሚዛን የሚያቀል ሁሉ ስህተት ይፈፅማል። ህብረት ቀዳሚ ነው። በግል አንድ ድርጅት ለብቻው ታግሎ ድልም ለመቀዳጀት የሚያስችል ሁኔታ የለም አልን እንጂ ሆኖ ቢገኝ እሰየውና ዕልልታችንን አንነፍገውም። ሰመረ ካሉ ግብሩን ያሳያሉ ነው ለነገሩ። ይህ በማይሆንበት ግን ለየግል ያቃተን በጋራ መገርሰሱ ብልህነት ነው። ስለዚህም ዛሬ ጊዜ ያለፈበትን በምርጫ እንሳተፋለን፤ አሜሪካን አይዟችሁ ብሎናል ወይም መሰል ሀገር ሳጂን ትግል ሳጂን አቅዋሞችን ወደ ጎን በመተው ተቃዋሚ ድርጅቶች ማድረግ ያለባቸው የሚከተሉትን መሆኑን ተጨባጩ ሁኔታ ይጠቁማል።

1. በህብረቱም ሆነ በሲቪክ ማህበራት በተጠራው መሰረት በሁሉን ድርጅቶች
አቀፍ ጉባዔ ተገኝቶ የጋራ ዕቅድ መንደፍ፤

2. ከወያኔ ፍትህ ወይም ዴሞክራሲ ይገኛል የሚለውን ለአንዴም ለሁሌም እርግፍ አድርጎ ጥሎ፤ ዕርቅና ሰላም ይወርዳል የሚባለውና ተሞክሮ ውድቅ ያደረገውን የተሳሳተ አቅዋም በመተው አገዛዙን በተቻለው መንገድ ሁሉ ታግሎ ለመጣል መነሳሳት ያስፈልጋል።

ዋናው ስራ ግን በሀገር ቤቱ መስክ ሁኔታው ግድ በሚለው ጥንቃቄና ምስጢራዊነት ህዝብን ለቁርጠኛው ትግልና ፍልሚያ ማዘጋጀት ነው። የተጀመረው ማዕቀብ በወያኔ ላይ መጠናከሩ፤ አገዛዙ ሚሌኒየም በሚለው ላይ ከቶም አለመሳተፉ፤ በአገዛዙ የማወናበጃው መሬት ተመሩ ነግዱ ሴራ አለመሳተፉ፤ሀገር ወዳዳዊ ክብርን መጠበቅ፤ ተቃዋሚ ድርጅቶችን የሚከፋፈሉትን ሁሉ መቃወምና ለአንድነት መቆም ያስፈልጋል።

የደረስንበት ቦታና የታሪክ አጋጣሚ ወሳኝ ነው። ሀገርን ማዳን ይቻላል ወይም ሀገራዊ ግዴታን ረስቶ ሀገርን ለወያኔ አሳልፎ መስጠትና ለጥፋት መዳረግ ይቻላል። ምርጫ አይሉት ምርጫ ነው። የሕዝብ ድርጅቶችና ሀገር ወዳዶች ያላቸው ምርጫ አንድ ነው-- የሀገር ጠላትን በቁርጠኝነት መታገል። ከስልጣን ማስወገድ። ኢትዮጵያን ማዳን። ሁላችንም የምንኮራባት ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ እውን ለማድረግ። ተጨባጩ ሁኔታ ግድ የሚለው ይህን ነው። ምን መደረግ አለበት ለሚለው ያለው አንድና ብቸኛ መልስ የመለስን አገዛዝ በሁሉም መስክ ታግሎ መጣል ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com